# የ"ወሃቢዝም" ፖለቲካዊ ዕውነታ እስከ የት ድረስ ነው?

**(ክፍል አንድ)**

*"አሁን ካለው ሁኔታ የምንረዳው አንዳንድ ሰዎች የራሳቸውን እምነት በሌሎች ላይ በግድ የመጫን ፍላጎትና አመለካከት መኖሩን ነው።"*

*-ተሰናባቹ በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ዶናልድ ቡዝ*

**ጀማል ኑሩ** 08/14/13

ይህን ጥቅሳዊ አባባል የወሰድኩት ሰሞኑን አይጋ ፎረም ድረ-ገፅ አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ አምባሳደር በነበሩት ዶናልድ ቡዝ አማካኝነት ተዘጋጅቶ ለዋሽንግተን የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የተላከን፣ ነገር ግን በምስጢራዊ መረቦች አማካኝነት አፈትልኮ የወጣን ሪፖርት ከ'ኢትዮ ዲያስፖራ ሬድዮ' በመውሰድ በድምፅ ካሰማን ፕሮግራም ላይ ነው። በፕሮግራሙ ላይ 'የፖለቲካዊ ኢስላም አጀማመር' በሚል ርዕስ በቀረበው የምስጢራዊ ሰነዱ ሪፖርት፤ አምባሳደር ቡዝ በሀገራችን የራሱን እምነት በሌሎች ላይ በመጫን 'እኔን ብቻ ተከተሉኝ' በማለት የሚታወቀው የሰለፊ ወይም የወሃቢ አስተምህሮት እንዴት እንዳቆጠቆጠ፣ በየትኞቹ ሀገራት እንደሚደገፍ፣ ሊያስከትል ስለሚችለው አደጋ፣ የአምባሳደሩ ምልከታና ኤምባሲው ከጉዳዩ አኳያ ስላከናወናቸው ተግባራት በስፋት ተተንትኗል—መወሰድ ስላለበት ተገቢ እርምጃም ጭምር።

ታዲያ ይህን ሪፖርት ሳዳምጥና በመግቢያዬ ላይ የጠቀስኩት ዓይነት የሚስተር ቡዝን ትክክለኛ ምስጢራዊ እማኝነትን ከፕሮግራሙ ስሰማ አንድ ማለፊያ ጥያቄ የአዕምሮዬን ጓዳ ሸው ብሎት አለፈ—"'የወሃቢይዝም' ፖለቲካዊ ዕውነታ እስከ የት ድረስ ነው?" የሚል። እናም በምስጢራዊ ሰነዱ አማካኝነት ይፋ ከሆነው ሪፖርት በስተጀርባ ያለውን የአመለካከቱን አስተምህሮት አደጋ ለማመላከት፤ የ"ወሃቢይዝም" ቡድንን ውስጣዊ ፍላጎትና ኢትዮጵያ ውስጥ ሊከውን የሚፈልገውን ጉዳይ በማጉላት፤ ቡድኑ አስተሳሰቡን

ፀረ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ማራመድ ያስችለው ዘንድ በመንግስት ላይ የሚያካሂደውን የማጥላላት ዘመቻና ሌሎች ጉዳዮችን የተመለከቱ ሰነዶችን በመፈተሽ እንደ አንድ ሙስሊም ዜጋ የበኩሌን ለማለት ወደድኩ–"ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም" እንዲል ብሂሉ።

የራሱን ፖለቲካዊ ፍላጎት በገንዘብ ኃይል ለማሳካት ማናቸውንም ኢስላማዊ ጉዳዮች እያነሳ በመንግስት አሊያም በገዥው ፓርቲ ላይ የሚለጥፈው የ"ወሃቢዝም" ቡድን፤ እስካሁን ድረስ የኢፌዴሪ መንግስት በህገ-መንግስቱ መሰረት ሀገራችን ውስጥ የሃይማኖት እኩልነትንና የእምነት ነፃነትን ለማረጋገጥ ያደረጋቸውን ሰናይ ጥረቶች በሸውራራ ዕይታ ብቻ የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህም ቡድኑ አስገራሚ በሆነ ሁኔታ "መንግስት በእስልምና ላይ ዘመቻ ከፍቷል" ከማለት አልተመለሰም፡፡

...ሆኖም በእምነቱ ውስጥ ያለን ሰዎች ይሁኑ ማንኛውም ሃይማኖቱን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው፤ አንድን ሀገር ለመምራት ከዜጎቹ ውክልና የተቀበለ መንግስት በየትኛውም እምነት ላይ የሚከፍተው አንዳችም ዘመቻ ሊኖር እንደማይችል ይገነዘባል፡፡ እንኳንስ በቀረፀው ህገ - መንግስት ላይ፤ መንግስት በሃይማኖት፣ ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ ሳይገቡ የሁሉም እምነት ተከታዮች የፈለጉትን ዓይነት እምነት ያለ ምንም ጫና በነጻነት የመከተል መብት እንዳላቸው የደነገገ እና በተግባርም የገለጸ መንግስት ቀርቶ፣ ሌሎች ህሊና ያላቸው ወገኖችም ቢሆኑ በየትኛውም ሃይማኖት ላይ ጥቃት የሚከፍቱበት አንዳችም ምክንያት ሊኖራቸው አይችልም፡፡

ይህ ሲባል ግን መንግስት ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታን ለማናጋት የሚጥሩ አክራሪዎችን ዝም ብሎ ይመለከታል ማለት አይደለም፡፡ በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች ሰርተው በውጤታቸው ተጠቃሚ መሆን እየቻሉ፣ እምነታቸውን እንደ ሸቀጥ ለውጭ ገበያ በማቅረብ የፅንፈኝነት ተግባርን የሚያከናውኑ ከሆነ፤ ይህን መሰሉን ፀረ ህገ -መንግስት አካሄዳቸውን እንዳላየ ሆኖ እጁን አጣጥፎ ሊቀመጥ አይችልም፡፡ ህግና ሥርዓትን የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ያለበት አካል ነውና፡፡

ዳሩ ግን ቡድኑ ራሱን ለመከላከል ሲል መንግስት በጥቂት ጽንፈኞች ላይ እየወሰደ ያለውን ህጋዊ ተግባር ልክ በእስልምና ሃይማኖት ላይ የተፈጸመ በማስመሰል ለማደናገር

ሞክሯል፡፡ ይህ ደግሞ “ምን ያለበት ዝላይ አይችልም” እንዲሉት ዓይነት ይትብሃል በቀጥታ በእስልምና ስም የመነገድ አስፀያፊ ድርጊት ነው፡፡ እርግጥ “ወሃቢዝም” በሀገራችን ውስጥ መንግስት አንዱን ሃይማኖት በመደገፍ ሌላውን መንቀፍ የሚችልበት አካሄድ የማይከተል መሆኑን ሊገነዘብ አይፈልግም፡፡ ምክንያቱም ይህን መሰሉ ተግባር የእያንዳንዱ ሃይማኖት ተከታዮችና ተቋሞቻቸው ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡

ታዲያ ቡድኑ ይህን ሃቅ ወደ ጎን በማለት ለራሱ የፖለቲካ ፍጆታ ሲል የሌለ ድርጊትን በማንቀለጻጸስ የመንግስትን ሰናይ ምግባሮች ለማጠልሸት መሞከሩ ሚዛን የሚደፋ አለመሆኑን መረዳት ያለበት ይመስልኛል፡፡ የቡድኑ ሌላኛው እምነት መንግስት “ወደ ትናንቷ ኢትዮጵያ ህዳሴ እንመልስ ማለት ማብዛቱ ያስጠረጥረዋል” በማለት ሃይማኖት ወደ ኋላ ይመለስ ከማለት አይመለስም የሚል ነው፡፡ ታዲያ ይህ ህዝበ ሙስሊሙን ለማደናገር የተሰደረው “የቆርጦ ቀጥሎች” ቡድን ምን እያለ ይሆን?–አዎ! “ወሐቢዝም” ፍላጎት በጥርጣሬ ላይ ቢመሰረትም መልዕክቱ ግን ግልጽ ነው፡፡

አንድም ሆን ብሎ የተባለን ትክክለኛ ጉዳይ በማጣመም የሌለ ጉዳይን በሙስሊሙ አህምሮ ውስጥ ለመሰንቀር ያለመ ሲሆን፣ ሁለትም ቡድኑ በተዘዋዋሪ መንገድ ኢትዮጵያ እንዳታድግ ያለውን የጽልመት ራዕይ እየነገረን ነው፡፡ እስቲ ሁለቱንም በየተራ እንመልከታቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መንግስት “የትናንቷ ኢትዮጵያ እንመለስ” ማለቱ የቡድኑ ጥቂት ተከታዮች እንደሚዘላብዱት፣ ከየትኛውም ሃይማኖት ጋር አንዳችም ቁርኝት የለውም፡፡ “የትናንቷ ኢትዮጵያ” ማለት በዓለም ላይ ገናና የነበረችና የስልጣኔ ማማ ላይ የወጣችውን የያኔዋን ኢትዮጵያ ነው፡፡

እናም አባባሉ ትላንት የነበሩት አበውና እመው የሰሩትን ታሪክ በማደስ፣ እኛም የማንነታችን መገለጫ የሆነውን ድህነትንና ኋላ ቀርነትን ድል ነስተን ታሪካችንን እናድስ ማለት እንጂ፣ ከሃይማኖት ጋር የሚያገናኘው አንዳችም ነገር የለም፡፡ እርግጥ ይህ ማንነትን የማደስ ተግባር ፍጹም የተረጋጋና ሰላማዊ ምህዳርን የሚጠይቅ በመሆኑ፣ በሃይማኖት ስም ለሚነግዱ አክራሪ ጽንፈኞች የሚመች አይደለም፡፡

በመሆኑም “ወሃቢዝም” ከወዲሁ ለራሱ የሚሆን መደላድል ለመፍጠር ሀገራችን እንዳትታደስ፣ አባባሉን ከሃይማኖት ጋር ቆርጦ በመቀጠል ለማጣበቅ መሞከሩ የሚገርም አይደለም– በህዳሴው ባቡር ላይ ማንኛውም አደናቃፊ እየተንጠባጠበ መውደቁ ስለማይቀር

ስጋቱ ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡ የአባባሉን ሌላኛ ገጽታ ስንመለከተው ደግሞ፤ የአባባሉ ባለቤቶች  ፖለቲካዊ ግብን አንግበው የተነሱ በመሆናቸው ከሀገራችን የልማት ዕድገት ጋር ሆድና ጀርባ መሆናቸውን በገሃድ እየገለጹልን ነው፡፡

እርግጥ ዕድገት ተረጋግጦ ማንኛውም ዜጋ በየደረጃው  ተጠቃሚ መሆን ሲጀምር፤ ለአክራሪነት የሚሆን የተመቻቸ ምህዳር ሊኖር አይችልም፡፡ ሁሉም የሀገሪቱ ህዝብ የተገኘው ልማታዊ ዕድገት የራሳቸው አጀንዳ ባላቸው ጥቂት ጽንፈኞች እንዲደናቀፍበት አይፈልግም፡፡ በመሆኑም የ"ወሐቢዝም" እፍኝ የማይሞሉ አራማጆች "ወጡ ሳይወጠወጥ፣ ወስከንቢያው ቂጢጥ" እንደሚባለው፤ ከወዲሁ ስለ ህዝቡ ማደግና መበልጸግ አሳስቧቸው ሁኔታውን አጣሞ በመመልከት ከሃይማኖት ጋር ሊያያይዙት መሻታቸው በእነርሱ ዓይን ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡ ምንም እንኳን በአብዛኛው ህዝብ ዕይታ ይህን መሰሉ ፀረ - ልማትና ፀረ- ዴሞክራሲያዊነት አስተሳሰብ የሰይጣን ተግባር መሆኑ የማያከራክር ቢሆንም።

የ"ወሐቢዝም" አስተሳሰብ አራማጆች ሀገራዊውን የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ከመንግስት ልሳኖች ጋር የሚጋጭ አስመስለው ሙስሊሙን ማህብረሰብ ለማደናገር ሞክረዋል፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል በመንግስትና በገዥው ፓርቲ ልሳናት ላይ የሚሰፍሩት እንደ "ሀገራችንን ከየትኛውም ወገን ለሚመጣ የዓለም አቀፍ የሃይልና የሃይማኖት ፉክክር ግንባርነት ማዳን የግድ ይኖርብናል" የሚለውንና ገዥው ፓርቲ እንደ መንግስት ኢትዮጵያን የአክራሪዎች አውድማ ለማድረግ ከሚንቀሳቀሱ ጽንፈኞች የመታደግ ግዴታውን በማንሳት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው በገጽ ሰባት ላይ እንደ ህዝብ በብድርና በእርዳታ አማካኝነት የተጫነብንን ሀገራዊ ውርደት በቁጭት ያወሳውን ጉዳይ በማይገናኝ ሁኔታ ቀጣጥሎ በመስፋት ለማሳየት ይሞክራሉ፡፡

የ"ወሃቢዝም" አቀንቃኞች ፖሊሲውን በመጥቀስ "ልማትና ዴሞክራሲን ለማረጋገጥ የውጭ ዕርዳታና ብድር ካልታከለበት ሊነቃነቅ አይችልም፡፡…ስለሆነም ብድሩንና ዕርዳታውን ለማግኘት ደጅ ጠኚ መሆን አለብን፡፡…" በሚል ከመንግስት ልሳናት ጋር ተጻራሪ አስተሳሰብን አስፍሯል ይላሉ፡፡ ዳሩ ግን ይህ አባባላቸው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውን ገለጻ የማያመላክት ብቻ ሳይሆን፤ ፖሊሲው ውስጥ የሌለ ሃሳብን ለማታለል ያካተተ ጭምርም ነው፡፡ ፖሊሲው በገጽ ሰባት ላይ "ሀገራዊ ውርደት እንደ ፖሊሲ መነሻ" የሚል ርዕስ ስር ገጽ ሰባት ላይ የሚለው "ልማትን ለማረጋገጥ የውጭ ዕርዳታ…" እንጂ፤

የ"ወሃቢዝም" አቀንቃኞች ሆን ብለው ያለቦታው ከሙብት ጋር ለማያያዝ የጨመሩት "ዴሞክራሲ" የሚል ነገር የለበትም፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ፅንፈኞቹ ከጽሑፉ በታች ቆርጠው ያስቀሩት ነገር ግን ብድርና ዕርዳታ "የሀገራዊ ውርደት፣ ሐፍረትና መሸማቀቃችን አንድ ምንጭ ነው" የሚለውን የፖሊሲውን ዋነኛ ሃሳብ የረሳ ነው፡፡ እነዚህ እውነታዎችም የወሃቢ አቀንቃኞች ለፖለቲካ ፍጆታቸው ሲሉ የሌለ ጉዳይን ከመጨመር እንኳን ወደ ኋላ የማይሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥልን ነው፡፡

ሌላኛው የቡድኑ ስህተት እንደ ለመደው አንድ ዓይነት ጉዳዮችን በግድ ለማለያየት የፈጠረው ዘዴ ነው፡፡ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የመንግስት ልሳናት "ሀገራችንን ከአክራሪዎች ፍልሚያ እንታደግ" ማለታቸው እና ፖሊሲው ስለ ሀገራዊ ውርደት ምንጮች ማውሳቱ የተለያዩ ነገሮች አይሉም– ሁለቱም አገላለጾች ከልማት አኳያ የራሳቸው የተመሳስሎ ያላቸው ናቸውና፡፡ ስለሆነም የመንግስትና የገዥው ፓርቲ ልሳናት 'ሀገራችን የማናቸውም ሃይማኖቶች ዓለም አቀፍ የሽኩቻ መድረክ መሆን የለባትም' ማለታቸውም ይሁን፣ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው ድህነታችንን እንደ ቁጭት በማውሳት 'ሀገራችንን ከብድርና ዕርዳታ ላቅቀን ለዘመናት አብሮን የኖረውን የተመጽዋችነት ስም እንቀይር' ማለቱ አንድና አንድ ናቸው፡፡ "ሰልቻም ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎም ስልቻ" እንዲል የሀገራችን ሰው፡፡

በሌለ ጭብጥ በማራገብ፣ ያልተጻፈን ፅሑፍ በመጨመር እንዲሁም የተፃፈን ቆርጦ በማውጣት ስልትን የሚከተለው የወሃ""ቢ ቡድን ፣ በራሱ ጊዜ ከፖሊሲው አንደኛ ጫፍ ወደ ሌላኛው እየተላጋ የሚሄድ ነው፡፡ በል ሲለው የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር የተዘጋጀውን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በሚያስገርም ሁኔታ ሃይማኖትን ለማዳከም የተዘጋጀ አድርጎ ያቀርባል፡፡ ምንም እንኳን እንዲህ ዓይነቱ ስሌት - አልቦ የግምት አስተሳሰብ የትም የማያደርስ ቢሆንም፤ ቡድኑ ግን ከየት እንዳመጣው ግልጽ ባልሆነ መልኩ ፖሊሲው እስልምናን ለማዳከም መዘጋጀቱን ያለ ሃፍረት ሊያስረዳ ይሞክራል፡፡

ለዚህም በፖሊሲው ላይ ያልሰፈረውንና ኢትዮጵያ በሱዳን ላይ እከተለዋለሁ ያላለችውንና ከዚያች ሀገር ጋር ያላትን ግንኙነት በማሳያነት ይጠቀማል፡፡ ማሳያው ግን ፖሊሲው "የግንኙነቱ ታሪካዊ ፋይዳ" በሚለው ርዕስ ስር፤ በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል ቀደም ባሉት መንግስታት ውስጥ የነበረውን "የጎሪጥ የመተያየት" አባዜ ለማመላከት

ከተጠቀሰው ውስጥ ተቀንጭቦ የተወሰደ ነው፡፡ አዲሲቷ ኢትዮጵያ በሱዳን ላይ የምትከተለወ አካሄድ አይደለም፡፡

የ“ወሃቢዝም” አራማጆችም እነርሱ ከሚከራከሩበት ጉዳይ ወረድ ብለው በገጽ 93 ላይ በፖሊሲው ላይ “ሱዳንን በተመለከተ ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ” የሚለውን የመንግስትን አቋም ሳይጠቅሱት ቢያልፉም፤ “በአፍሪካ ቀንድ የላቀ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባን በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል ላለው ግንኙነት ነው።... ከጎረቤት ሀገሮች ጋር፣ በተለይም ከሱዳን ጋር ጠንካራ ግንኙነት የመመስረት ፖሊሲ ልንከተል ይገባል፡፡....” በማለት አጽንኦት ሰጥቶ ያብራራል። ይህም የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ወንድም ከሆነው የሱዳን ህዝብና ከሀገሪቱ መንግስት ጋር ዛሬ ላይ ለደረሱበት ጠንካራ ግንኙነት መሰረት የሆነ እንጂ “ወሐቢይዝም” እንደሚያደናግረው በጥርጣሬ ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡

የኢፌዴሪ መንግስት እንዳለፉት ፀረ - ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶች ጎረቤት ሀገሮችን በጥርጣሬ የሚመለከት አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ በጎረቤት ሀገራት ውስጥ ቀደም ሲሉ ሲንከባለሉ የነበሩ ችግሮችን ሰላምን መሰረት አድርጎ የጋራን ጥቅምን ተመርኩዞ እየፈታ የመጣና ሀገራቱ ከዕድገታችን ተቋዳሽ እንዲሆኑ ያደረገ ነው፡፡ የወሃቢ ቡድን “በአቦ ሰጥ” እንደሚያስወራው፤ የኢትዮጵያ መንግስት የክርስትና ሃይማኖትንም ሆነ እስልምናን የሚከተሉ ወገኖችን የሚጠራጠር ቢሆን ኖሮ፣ ዛሬ ላይ የሁለቱ ሱዳኖች የችግር ወቅት ምርጫ ኢትዮጵያ ባልሆነች ነበር፡፡

ግና እውነታው የተገላቢጦሽ በመሆኑ የየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ጎረቤት ሀገር ችግር ሲያጋጥመው ሁኔታውን ለመፍታት ሀገራችን ለችግሩ ፈጥና እንድትደርስለት ይሻል፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ መንግስት ከሚከተለው የሠላም፣ የገለልተኝነትና የጋራ ተጠቃሚነትን ባረጋገጠው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው አማካኝነት ነው፡፡ እናም የወሃቢው ቡድን የህልም ቅዠት ፍላጎት ከንቱ መባዘን ከመሆን የሚዘል አይሆንም – ከነባራዊው ሃቅ ጋር ፈጽሞ የሚተዋወቅ አይደለምና፡፡

ማንኛውም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው፤ በ1995 ዓ.ም ይፋ የሆነው የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በዋነኛነት የተቀረጸው ሀገራችን ከሌሎች ሀገሮች ጋር የሚኖራት ግንኙነት ብሎም ሊያጋጥሙን የሚችሉ ጉዳዮችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ

የሚተነትን ነው፡፡ እርግጥ በሰነዱ ላይ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ሀገራችን የማንኛውም ሃይማኖት አክራሪነት ስጋት ሊያጋጥማት እንደሚችል ተጠቁሟል፡፡

የወሃቢው ቡድን ይህን ውጤታማ ሰነድ በቅዥት ዓለም ውስጥ ሆኖ አራምባና ቆቦ እየረገጠ በሚዘላብድ ብዕሩ ለማየት ቢሞክርም፤ ሃቁ ግን በተጨባጭ መሰረቶች ላይ ተመርኩዞ ከየትኛው ሀገር ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖረን እንደሚችል በአስተማማኝ ሁኔታ ያሳየ ነው። ሌላው ቀርቶ የሃይማኖት አክራሪነት እንደሚጋጥመን አርቆ የተመለከተ መሆኑን የዛሬዎቹ የወሃቢያ ጽንፈኞች ህያው ምስክር ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

እናም 'ለምን ታወቀብን' በሚል እሳቤ ሰነዱን ቀንድና ጭራ እያበቀሉለት ብሎም ከማይገናኝ ጉዳይ ጋር በግድ በማቆራኘት ለማብጠልጠል መሞከር የትም የሚያደርስ አይደለም–ሃይማኖታቸውን ለባዕዳን የሸጡ አክራሪዎች አንደሚመጡ አስቀድሞ ተንብዩዋልና፡፡ የወሐቢያው ቡድን አንዱን አንስቶ ሰይጨርስ ወደ ሌላ የሚሸጋገር ነው፡፡ ከአዲስ ራዕይ ወደ ውጭ ጉዳይ ፖሊሲው ያደረገውን የዝላይ ቅጥፈት ስብከት ሳይጨረስ፣ ዘሎ ወደ ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በመንጠልጠል መስሪያ ቤቱ ያልተቋቋመበትን ዓላማ ራሱ እየሰጠው አስገራሚ ትንታኔዎችንም ያቀርባል፡፡

እንደሚታወቀው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ  በህግ ከተሰጠው ስልጣን ውስጥ አንዱ፤ በመላ ሀገሪቱ ዘላቂ የሆነ ሰላምን ለማስፈን አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በህገ -መንግስቱ አግባብ መሰረት እንዲፈቱ ማድረግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ 'የወሐቢያው ሰነድ" ለሰሚው ግራ በሚያጋባ ሁኔታ 'አህባሽን እያስፋፉ ነው' በማለት ይከሰዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ በዋቢነት የሚያቀርበው 'በመስሪያ ቤቱ ውስጥ አንድም ሙስሊም የለም' የሚል አስቂኝ ምክንያት በማቅረብ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ቀደም ሲል ለጥቀስ እንደሞከርኩት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አለመግባባቶችን የሚፈታ መንግስታዊ ተቋም እንጂ፤ የትኛውንም ሃይማኖት ሆነ የእምነት ወገን የመደገፍም ይሁን የማጣጣል አካሄድን በግብነት የሚከተል አይለደም፤ሊከተልም አይችልም፡፡ ምክንያቱም መንግስትና ሃይማኖት በተለያዩበት ሀገር ውስጥ እንዲህ ዓይነቱን ኢ- ህገ-መንግስታዊ ተግባርን የሚፈጸም የመንግስት ተቋም ሊኖር ስለማይችል ነው፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ከመሬት ተነስቶ አንድ መንግስታዊ ተቋም ላይ ጣትን መቀሰር፤ መስሪያ ቤቱ በሀገሪቱ ውስጥ የሚፈጠሩ ጊዜያዊ አለመግባባቶችን ለማርገብ

የሚያደርገውን ጥረት ላለመቀበል ሆን ተብሎ የሚኒስቴሩን ስም ለማጥፋት የተዘየደ መላ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ምንም እንኳን “ወሐቢይዝም” በመስሪያ ቤቱ ላይ የዶለተው ሴራ ውኃ የማይቋጥር ቢሆንም፡፡

እንዲያው ለመሆኑ ቡድኑ መስሪያ ቤቱ ‘ነባሩን እስልምና እያስፋፋ ነው’ ሲሉ ከቶ ምን ማለት ይሆን?፣ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሙስሊም ሲከተል የኖው በሀገሪቱ ውስጥ የተስፋፋውን ነባሩን እስልምና መሆኑ እየታወቀ፤ እንደምን የተስፋፋውን መልሶ ሊያስፋፋው ይችላልል?’ የሚል ጥያቄ ቢነሳ፤ ቡድኑ ምላሽ ሊኖረው አይችልም –በቀጥታ ንግግር ነባሩ እስልምና ‘መወገድ አለበት’ ለማለት ካልፈለገ በስተቀር።

ይሁንና ይህ ዓይነቱ የራስን አስተሳሰብ በሌሎች ላይ በኃይል ለመጫን መሞከር አካሄድ ደግሞ የአክራሪዎች ፀረ - ዴሞክራሲያዊ ምልከታ በመሆኑ በማንኛውም ወገን ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ኸረ ለመሆኑ የወሐቢያው ቡድን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን በመጥቀስ “በውስጡ አንድም ሙስሊም የለም” ሲል ምን እያለን ይሆን?– እንደሚታወቀው በማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት የሁሉም ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ዜጋ በብቃቱና በክህሎቱ የሚመደብበት እንጂ፤ ሃይማኖትዊ ተቋም አይደለም፡፡

እናም ሙስሊምም ይሁን ሙስሊም ያልሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአቅሙና በችሎታው ተመድቦ መስራት ይችላል፡፡ በእኔ እምነት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የስራ ክፍሎች ውስጥ ‘ሙስሊሞች የሉም” ብሎ መናገር የእብድነት ያህል የሚቆጠር ነው – ደግሞም ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ግለሰቦች እንደነገሩኝ በርካታ ሙስሊሞች በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ሊኖሩ አሉ። ታዲያ እዚህ ላይ ይህ የወሐቢያ ጭፍን መላ - ምት የሚያመላክተን አንድ ጉዳይ መኖሩን ውድ አንባቢዎቼ እንደሚገነዘቡት እርግጠኛ ነኝ፡፡ ይኸውም ወሐቢያ ሌሎች የሀገሪቱ ሃይማኖቶች ሁሉ ከስመው፣ እርሱ በአስገዳጅነት አመለካከቱን በጉልበት በመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ለማስረጽ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው በአደባባይ እየነገረን መሆኑ ነው፡፡

ሌላው ቀርቶ ለአብነት ያህል የተለያዩ የሃይማኖት ተከታዮች የሚገኙበትን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ተቀጣሪዎች ያለ አንዳች ይሉኝታ “ክርስቲያኖች ናቸው” ብሎ መፈረጅ፤ አክራሪው ቡድን በሌሎች ሃይማኖቶች ላይ ያለው ጥላቻ ምን ያህል ስር የሰደደ እንደሆነ በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን መሰሉ የሌሎች ዜጎችን

እምነት በአደባባይ ለመድፈቅ መሞከር፤ በዴሞክራሲያዊቷ ሀገራችን ውስጥ ፈጽሞ ቦታ የሌለው መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ በምደባ መልክ 'ሙስሊሞች መኖር አለባቸው' በማለት ለማላዘን የሚሞክረው ሰነዱ፤ የጥያቄው መነሻ ግልፅነት አጠያያቂ አይደለም፡፡ አዎ! እርግጥም ጥያቄው 'የመንግስት መስሪያ ቤቶች በሃይማኖታዊ አሰራር መተካት ይኖርባቸዋል' የሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የመንግስትና የሃይማኖት መለያያ ገመድን በመበጠስ ሁለቱንም አንድ የማድረግ ቀቢጸ-ተስፋ ነው፡፡ ማሳረጊያውን እስላማዊ መንግስት መመስረት ያደረገ ተልዕኮ– ለዚያውም መንግስትም ሆነ ተቋማቱ ብሎም መላው የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሸሪዓ ህግ እንዲተዳደሩ የማድረግ ፍላጎትን ያነገበ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ተግባር፡፡

ለነገሩ ይህ በጥቂት ፅንፈኞች የሚቀነቀነው የቡድኑ አስተሳሰብ ከቁራ ጩኸትነት የሚዘል አይደለም፡፡ ምክንያቱም እኔን ጨምሮ አብዛኛው ሙስሊም እነዚህ ወገኖች በመራር ትግልና በወድ የህዝብ ልጆች መስዋዕትነት የተገኘውን ህገ - መንግስት ለመናድ የተሰለፉ ኃይሎች መሆናቸውን ጠንቅቀን ስለምናውቅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ህገ- መንግስቱ ያጎናፀፈንን የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ትሩፋቶችን የኋሊት የሚቀለብስ ነው፡፡ በመሆኑም የእነዚህ ወገኖች እኩይ ፍላጎት እንዲመክን እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ከመካከላችን ልንነጥላቸው ይገባል፡፡

እርግጥ የእነዚህ ፅንፈኞች ፍላጎት የፖለቲካ ስልጣን ምኞት እንጂ፤ ሃይማኖታዊ አለመሆኑን ቢያንስ ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው በመንግስትና በተቋማቱ ላይ የሰነዘሩትን ፖለቲካዊ እሳቤ ማጤን ብቻ በቂያችን ስለሚሆን ነው፡፡ እናም ፖለቲካዊ ሽኩቻ በፖለቲካ መድረክ እንጂ፤ ሃይማኖትን እንደ መከላከያ ምሽግ በመቁጠር መከናወን እንደሌለበት በግልፅ በመንገር ሚናቸውን እንዲለዩ ማድረግ ከሁሉም ህዝበ-ሙስሊም የሚጠበቅ ተግባር መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡…ውድ አንባቢዎቼ በክፍል ሁለት ፅሑፌ ላይ የ"ወሃቢይዝም" ቡድንን ውስጣዊ ፍላጎቶችን እና ሌሌች ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰቦቹን ላስነብባችሁ እሞክራለሁ።…